# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP

ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም.

### ታላቅ የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ በፍራንክፈርት ከተማ ጀርመን

ከተመሰረተ 41 አመቱን በማስቆጠር ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን ለመጎናፀፍ፡ መሰረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹንና የሀገሩን ሉአላዊነት ለማስከበር በሚያደርገው የትግል እንቅስቃሴ በግንባር ቀደምትነት የበኩሉን አስተዋፅዖ በፅናት እያበረከተ ይገኛል። ላለፉት 22 አመታት በወያኔ ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝ የተነሳ ሕዝባችን በአሁኑ ወቅት ከሚገኝበት እጅግ አሳሳቢና አሳዛኝ ሁኔታ በኢትዮጵያዊነታቸው በእጅጉ የፀኑና ለሕዝባቸው ቀናኢ የሆኑ እንደ ኢሕአፓ የመሰሉ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ከምንጊዜውም በበለጠ ትግሉን የመምራት ኃላፊነት የሚጠበቅባቸው ለመሆኑ የምንገኝበት ሁኔታ የሚያመለክተው እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ ከፍተኛ መስዋዕትነን እያስከፈለ በተለያየና ሁለገብ በሆነ መልክ የሚደረገውም ትግል ስኬታማ ይሆን ዘንድ  መጠናከርና መስፋፍት እንዳለበት ለክርክር የሚጋብዝ አይደለም። ይህንን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ደግሞ እነዚህ ድርጅቶች ከሕዝብ ጋር በተለይም የወደፊት ሀገር ተረካቢ ከሆነው ወጣት ትውልድ ጋር መወያየትና የጋራ ግንዛቤ ለማግኘት በመጣር ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት መግፋት የግዴታ እንደሚል ግልፅ ነው።

በመሆኑም በጀርመን ሀገር የሚገኙ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች፡

ሀ. የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት ጓድ ዶ/ር ዘነበ ተሾመ፡
ለ. የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ፕሬዘዳንት የሆኑት የተከበሩ አቶ አሊ ሁሴን፡
ሐ. የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ በአውሮፓ ተወካይና
መ. እንዲሁም አንዲት ወጣት እህት ሴት በእንግድነት በሚገኙበት፡-

1ኛ. በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ሁኔታ፡
2ኛ የወጣቱና የሴቶች ሚና በሕዝባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ፡
3ኛ የወቅቱ የፖለቲካ፤ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ ላይ በመንተራስ ኢሕአፓ ስለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ በአውሮፓ እያደረጋቸው ያሉትን እንቅስቃሴዎች በመቀጠል በቅርቡም በጀርመን ህገር ከሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ጋር ሰፊና ጥልቅ ውይይት ለማድረግ ቀጣይ ሕዝባዊ ስብሰባ በፍራንክፈርት ከተማ ያዘጋጀን በመሆናችን በዚህ ዝግጅታችን እንድትገኙልን በትህትና እንጋብዛለን።

| | |
|---|---|
| ስብሰባው የሚካሄድበት ቀን | ቅዳሜ ኦገስት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. |
| ሰአት | ከ ቀኑ 13:00 ሰአት እስከ ምሽቱ 19.:30 |
| ቦታው | Jugendherberge Frankfurt<br>Deutschherrnufer 12<br>60594 Frankfurt |
| ስለ ዝግጅቱ የበለጠ ለማወቅ | 0152 — 204074821<br>0173 — 421 2622<br>0152 — 1386 5107 ይደውሉ። |

EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645